# የኢሳያስ (የሸአቢያ) እስታራተጂ ፤ ኢትዮጰያን ለመታደግ ወይስ እንደገና ለመግደል?

ከአክሊሉ ወንድአፈረው

የተለያዩ ድርጅቶች የወያኔ/ ኢህአዴግን መንግስት በትጥቅ ሀይል ለማስወገድ በአስመራ ስልጣን ከያዘው ሻቢያ ጋር መቀራረብና ተባብሮ መስራትን መርጠዋል። ይህን በተመለከተ ባንድ በኩል የወያኔ/ኢህአዴግን የግፍ ስርአት ለማስወገድ ከማንም ጋር ቢሆን ማበር አስፈልጊ ነው የሚሉ ሲኖሩ ሌሎች ደግሞ የወያኔን የግፍ ስርአት ማስወገድ አስፈላጊ ሲሆን ሻቢያ ኢትዮጵያን በተመለከተ የሚከተለው ፖሊሲ በብሄራዊ ጥቅማችን ላይ እና በመጻኢው ነጻነታችን ላይ እጅግ ታላቅ አደጋን ስለሚያስከትል ድንገት ብቅ ያለው ተቋርቋሪነት ከምን የመነጨ እንደሆነ ጠንቅቆ መረዳትና ታላቅ ስህተት ከመፈጸም መታቀብ ያሻል ይላሉ::

በዚህ ጽሁፌ  የሻቢያ "ለኢትዮጵያ ተቆርቋሪነት" በተግባር ሲታይ ምን ማለት እንደሆነ ለማሳየት በጥቂት ውሱን ጉዳዮች ላይ በማተኮር ያለኝን አመለካከት አካፍላለሁ።

## <u>የኢትዮጵያ አንድነትና የአፋር ህዝብ አበሳ</u>

የሻብያ ፖለቲካ አልፋና ኦሜጋ የኤርትራን ተወላጆች ከሌላው ኢትዮጵያዊ በተጻራሪነት እንዲቆሙ ለማድረግ. "እኛና እነሱ" የሚል የልዩነት ድንበር በማበጀት በጥርጣሬ በጥላቻና በፍራቻ እንድንተያይ ማድረግ ነው። በዚህ ጥረቱ ውስጥ  መጀመሪያ በሻቢያ ውስጥ ቀጥሎም ሰፋ ብሎ በኤርትራ ማህበረሰብ ውስጥ የኢትዮጰያዊነትን ስሜት ያሳዩትን ሁሉ በመግደል በማሰቃየትና ከድርጅቱ በማባረር ከኢትዮጵያ ጋር የሚታይን ማንኛውንም ንክኪ ለማጥፋት ሲጥር እንደቆየ እጅግ ብዙ ታሪካዊ መረጃወች ያመለክታሉ።

በመለሰ ዜናዊ ተባባሪነት "ነጻነት " ካወጀና አስመራ ላይ መንግስት ከመሰረተ በኋላም ይህንን የኢትዮጰያዊነት ስሜት በኤርትራ ውስጥ የሚቀሰቅሱ፣ ሁኔታወችን እየለቀመ ከስራቸው ለማድረቅ ሞክሯል። ከህወሀት ጋር ግጭት ውስጥ ከገባ ወዲህ ደግሞ "ተቃዋሚውን አግዛለሁ፣ የኢትዮጵያ ጉዳይ አሳሰቦኛል" እያለ በሚለፍፍበት ሰአት ሳይቀር በጉልበት በያዘው ግዛት እና አፍኖ በሚገዛው ህዝብ ውስጥ የኢትዮጵያዊ ስሜትን ይቀሰቅሱብናል፣ የጀመርነውን የመከፋፈል ፕሮጀክት "ይበክሉብናል" ብሎ የሚጠረጥራቸውን ሁሉ በአይነ ቁራኛ ይከታተላል አስፈልጊ ሲሆንም ከስም ማጥፋት እስከ ህይወት ማጥፋት የሚደርስ እርምጃ ይወስዳል።

በዚህ አንጻር  ሻቢያ ከፍተኛ ሰጋት አድርጎ ከሚከታተላቸው የተለያዩ ክፍሎች ውስጥ አንዱ ከአፋር ማህበረሰብ ጋር የሚያያዝ ማንኛውንም ጉዳይ ነው።

የአፋር ማህበረሰብ ተወላጅ የሆኑት ታላቁ ኢትዮጵያዊው መሪና አባት ቢትወደድ ሱልጣን አሊሚራህ ሀምፍሬ ደግመው ደጋግመው እንዳሉት የአፋር ማህበረሰብ ኢትዮጵያዊነቱ ላይ ቅንጣት ያህል  ጥርጣሬ የሌለው (የደረሰበት ያስተዳደርና ሌላም በደልና ችግር እንዳለ ሆኖ) በሌላው ኢትዮጵያዊ ዘንድም እንዲሁ ከፍጹም ኢትዮጵያዊ ወንድምነት/እህትነት ውጭ የማይታይ ህዝብ ነው። ይህም በመሆኑ በሻቢያ አይን ኢትዮጵያን የባህር በር በማሳጣት ጉሮሮዋን አንቆ ለመኖርና ቢችል የርሱ ጥገኛ ለማድረግ ባለው ፍላጎት ጎዳና ላይ ዋነኛው እንቅፋት ተደርጎ መታየቱ አልቀረም።ይህ ደግሞ አሁን የተጀመረ ሳይሆን ሻቢያ ከደርግ ጋር ይፋለም በነበረበት ወቅትም የውስጥ እግር እሳት ሆኖበት የቆየ ሀቅ ነው።

እንደ አውሮፓ አቆጥጥር በ1991 አዲስ አበባ ላይ በተደረገው ጉባኤ ኢትዮጵያን የመከፋፈል አጀንዳ እየተጠነጠነ እንደሆነ የተረዱት ታላቁ ኢትዮጵያውዊ አባት ቢትወደድ አሊሚራህ ሀምፍሬ ይህን ሴራ ለማጋለጥ ደጋግመው እጃቸውን በማውጣት ለመናገር ፈቃድ ቢጠይቁም በስብሰባው ሊቀመንበር እድል ተነፍገው ነበር:: በመጨረሻም የድምጽ ማጉያውን  በግድ ነጥቀው "በኔ አመለካከት ይህ ጉባኤ የተሰበሰበው ኢትዮጵያን ለመበታተን ሳይሆን፡ እኩልነትን፡ፍትህንና  መልካም  አሰተዳደርን  ለሁሉም  ኢትዮጵያዊ  እንዴት  እንደምናሰገኝ  ለመመካከር  ነው::

የኢትዮጵያ ህዝብ ከዚህ ጉባኤ የሚጠብቀውም ውጤት አዲስ መንግስትና ዴሞክራሲን እንጂ ሁለት ቦታ የተከፈለች ሀገርን አይደለም”: ብለው ተናገሩ:: በዚህ ጊዜ ነበር የሻቢያ መሪ ኢሳያስ አፈወርቂ በቁጣ ስብሰባውን ረግጠ የወጣው::. ( Life History of Sultan Alimirah By Kadafo Hanfar, 2013, Pages 15 , Author House, LLC, Bloomington, IN)

በተጭማሪም የቢትወደድ ልጅ የተከበሩት መሀመድ አሊሚራህ ኤርትራን ከኢትዮጵያ የመለየት ሂደትን በተመለከተ “እኛ የኤርትራን የራስን እድል በራስ መወሰን አንቃወምም። በተመሳሳይ ሁኔታም የአፋር ህዝብ የራሱን እድል በራሱ የመወሰን እድሉ እንዲከበር እንሻለን። የራሳችንን ጉዳዮች ራሳችን እንወስናለን፣ ራሳችንን እናስተዳድራለን፣ ራስ ገዝ የሆነ የአፋር ክልልም አፋሮች በምንኖርበት ቦታ እንመሰርታለን። በኤርትራ አስተዳደር ክልል ውስጥ የሚኖረውም የአፋር ህዝብ በኢትዮጵያ ውስጥ ከሚገኙት አፋሮች ጋር ወይንስ ተለይቶ በኤርትራ ውስጥ ለመኖር እንደሚፈልግ እሱ ራሱ መወሰን አለበት” በማለት እቅጩን አስረግጠው ተናግረዋል።
(Afar Sultan insists on the right of his people in both Eritrea and Ethiopia to voice on Uniting. Life History of Sultan Alimirah, By Kadafo Hanfar Page 11, Author House, LLC, Bloomington, IN )

ይህንን የአፋር ህዝብ ፍላጎት ያወቀው ሻአቢያ አስመራ ላይ ስልጣን ከያዘ ጊዜ ጀምሮ የአፋርን ህዝብ ለይቶ ከፍተኛ ጥቃት አድርሶበታል፤፡ ይህ የተነጣጠረ ጥቃት ብዙ ገጽታወች ያሉት ነው። በአንድ ጽሁፍ ላይ እንደተገለጠውም ባሁኑ ሰአት “ በመላው ኤርትራ ካሉት ማህበረሰቦች ውስጥ አፋሮች በልማት እጅግ የተበደሉ ናቸው። በተጨማሪም ሌላው ቀርቶ በሻቢያ ትግል ውስጥ ተሳታፊ የነበሩት የአፋር ተወላጆች ሳይቀሩ ከመጀመሪያው አንስቶ የድብደባ እስራት፣ ግድያና “መሰወር” እንዲሁም የሌሎች ኢሰብአዊ ተግባሮች ሰለባ ናቸው” (QAFARMAROO,2008).

የኢትዮ ኤርትራ ጦርነት መጀመርም ለአፋር ህዝብ እጅግ የከፋ የስቃይ ዘመንን አስከትሏል። ከሽአቢያ ጎን ቆመው እየተዋጉ የነበሩ የአፋር ተወላጆች ሳይቀሩ “የኢትዬጵያ ሰላዮች” ተብለው በመጠርጠር ከፍተኛ አደጋ ደርሶባቸዋል። ጦርነቱ ከተቋጨ በሓላም የሻቢያ መንግስት በአፋሮች ላይ በማነጣጠር የከፈተው መጠነ ሰፊ እስራት ኤርትራን ጥለው ወደ ኢትዮጵያ ፣ ጅቡቲ፣ የመንና ሱዳን እንዲሰደዱ አስገድዷቸዋል። (APDA, February 4th, 2007; Medhane, October 2008).

ሻቢያ የአፋርን ተወላጆች (እንደ ኢሮብ፣ ኩናማ ወዘተ) ኤርትራን ከሌላው ኢትዮጵያ ጋር የሚያያይዝ አንዱና ዋነኛው ድልድይ፣ እንደሆነ ጠንቅቆ ያውቃል:: ይህ ደግሞ የሻቢያ መሪወች ከሚያልሙት ከፋፋይ አካሄድና የኤርትራን ድንበር እነሱ በፈለጉት መሰረት ለማስከለል ካላቸው ፍላጎት ጋር ግንባር ለግንባር ይላተማል:: ይህ ነጥብ (ድንበር ጉዳይ) ሻቢያ ከማንም ጋር በሚያደርገው ግንኙነት ውስጥ በግድ ያላንዳች ጥያቄ እንዲቀበሉት የሚያደርገው ጉዳይ ነው:: ከህወሀት ጋር ለመታረቅም ሻቢያ የሚጠይቀው በዋናነት ይህንኑ ነው።

ይህም በመሆኑ ሻቢያ በሚያገኘው አጋጣሚ ሁሉ የአፋርን ህዝብና ከአፋር ንቅናቄ ጋር የተዛመደን ሁሉ ከቻለ ለማጥፋት ካልቻለ ለማዳከም በተጨማሪም ከሌላው ኢትዮጵያዊ ጋር እንዳይደጋገፍና የተነጠለ እንዲሆን በተጠናከረ መልኩ ሙከራ ያደርጋል።

በዚህ አኳያ የሻቢያ የውጭ ጉዳይ መስሪያ ቤት ሰራተኛ የሆነው ተስፋዬ ገብረአብ የአንዳርጋቸውን መታሰር እስመልክቶ ባሰራጨው ጽሁፍ የአፋርን ንቅናቄ እንዴት ለማጥቀር እንደሞከረና ከሌላው ኢትዮጵያዊ ጋር እንዴት ለማለያየት እንደጣረ የሚከተለውን ፤ለአብነት እንመልከት።

በዲሰምበር 2014 በተለያዩ ድረገጾች እንዲሰራጭ በሆነው “አንዳርጋቸው ፅጌ እንዴት ተያዘ”? http://www.zehabesha.com/amharic/archives/37080 በሚለው ጽሁፉ ላይ ተስፋይ ገብረአብ (ሻአቢያ) “አፋሮች የማይታመኑ የወያኔ ሰላዮች” ናቸው የሚለውን መርዝ እንደሚከተለው ይነግረናል፡

> *“በአንድ ወቅት ግንቦት 7 ከነ ነአምን ዘለቀ እና ከአንድ የሆነ የአፋር ድርጅት ጋር ውህደት ነገር መፈፀማቸውን በዜና ነግረውን ነበር። ከውህደቱ በሁዋላ ብዙም የተወራ ነገር ሳይኖር ነገሩ ተድበሰበሰ።*

*ነአምን ዘለቀ ከግንቦት 7 ጋር አብሮ ሲሰራ ስመለከት ግን አፋሮቹም ሆነ እነ ነአምን ጠቅልለው ግንቦት 7 ውስጥ ገብተዋል የሚል ግምት ወሰጄ ነበር። የአንዳርጋቸው የመያዝ ሂደት ከዚያ ሳይጀምር አልቀረም።*

*አንዳርጋቸው ከአፋሮቹ የፖለቲካ ድርጅት ጋር ግንኙነቱን አጥብቆ ቀጥሎ እንደነበር አውቃለሁ። ምን እንደሚሰራ ግን ፈፅሞ ነግሮኝ አያውቅም። በመካከሉ ሆላንድ ሳለሁ ከግንቦት 7 ሰዎች በኩል የሾለከ የሚመስል ወሬ ሰማሁ። ይህም ወሬ ለስራ ተብሎ 30 ሺህ ዶላር ተሰጥቶት ወደ የመን የተላከ አንድ አፋር የመሰወሩ ወሬ ነበር። ወሬው በሰፊው የተሰራጨ አልነበረም። እጅግ በጣም ጠባብ በሆነ ቀዳዳ ነበር የሰማሁት። ይህ ወሬ ሲመዘን ተራ ወሬ ሊመስል ይችላል። አፋሩ ገንዘብ መያዙ በርግጥ መረጃውን ከፍ አድርጎታል። ከገንዘቡ በላይ ግን "የመን" የሚለው መረጃ ክብደት ነበረው። ግንቦት 7 የመን ላይ ትኩረት ማድረጉ ትልቅ መረጃ ነበር። አፋሩ የመን-ሰንአ ሲደርስ ተሰወረ። ከዳ ወይስ ተያዘ? አይታወቅም። ከድቶም ሆነ ተይዞ ወያኔ እጅ ገብቶ ሊሆን እንደሚችል ግን መገመት ይቻል ነበር። ይህ ከሆነ የግንቦት 7ን የተደበቀ ፍላጎት ወያኔ አውቶአል ማለት ነው።*

*ግንቦት 7 ምን እንደሚፈልግ ወያኔ ካወቀ፣ የግንቦት 7ን ፍላጎት ለማጥመጃ ሊጠቀምበት ይችላል። ቀላል ጉዳይ አይደለም። ግንቦት 7 የመን ላይ ምንድነው የፈለገው? ከስደተኞች መካከል ታጋዮችን መመልመል?*

*የተመለመሉትን ደግሞ ወደ ተከዜ በረሃ ማሻገር? ይህን ስራ ለማከናወን ብዙ ገንዘብ ይጠይቃል። ውድ ነው። ከሁሉም በላይ ግን ይህን ስራ ለመስራት የሚችል፣ አላማ ያለው ብቁ ሰው የመን ላይ ማግኘትን ይጠይቃል። አፋሩ ገንዘብ ይዞ የመን ላይ ከተሰወረ በሁዋላ አንዳርጋቸው ተሰፋ ቆርጦ ጉዳዩን ይተወዋል ተብሎ አይገመትም። እንደገና ይሞክራል። ወያኔዎች በዚህ በአንዳርጋቸው ዳግማዊ ሙከራ ጊዜ የራሳቸውን ሰው የመን ላይ አስቀምጠው አንዳርጋቸውን እንዲገናኘው አድርገው ይሆን? አንዳርጋቸው በረጅም ሂደት ወያኔዎች ያዘጋጁለትን ሰው እንደራሱ ሰው በማመን ለግንቦት 7 አባልነት በምስጢር መልምሎት ይሆን? እና በረጅም ጊዜ ሂደት አንዳርጋቸው ወያኔዎች ባዘጋጁለት ወጥመድ ውስጥ ሰተት ብሎ ገብቶላቸው ይሆን? ማለትም አንዳርጋቸው እነዚያ አባላቱን ለማነጋገር፣ አሊያም ታጋዮቹን ወደ ተከዜ ለማሸጋገር እንዲቻል አንዳንድ ጉዳዮችን ለመፈፀም በምስጢር የመን ገብቶ ለመውጣት ሞክሮ ይሆን?*

*ጥያቄዎቹ "አንዳርጋቸው እንዴት ተያዘ?" ለሚለው ጥያቄ ፍንጭ ሰጪ ሊሆኑ ይችላሉ። ቀጥተኛ መረጃ ያለው አካል የተፈፀመውን በዝርዝር እስካልነገረን ድረስ ከምናውቀው በመነሳት ለመገመት እንገደዳለን"።*

http://www.zehabesha.com/amharic/archives/37080#sthash.3T3Dy83Q.dpuf

ባጭሩ በአንዳርጋቸው መታሰር ዋና ተጠርጣሪው "አፋር" ነው ፤ አስመራ ከገባው ግንቦት ሰባት ጋር ግንባር የፈጠረው የአፋር ድርጅትም "የከሀዲ መሸሸጊያ፣ የወያኔ ጠቋሚወች ምሽግ ነው" ይላል ተስፋየ /ሻቢያ።

ይህ ነው የሻአቢያ ዋናው መልእክት፡፣ቅንጣት ታህል በኢትዮጵያዊነታቸው ላይ አላወላዳ የሚሉትን፣ ዛሬ ባይሆን ነገና ተነገ ወዲያ "ነገር ያመጡብኛል" የሚላቸውን ማጥቆርና ማስወገድ የሻአቢያ ዋነኛ ተልእኮው ነው። አጋጣሚውን ተጠቅሞ ሻቢያ "አፋሮችን አትመኗቸው" የሚለውን መርዘኛ መልእክቱን በኢትዮጵያውያን መሀል አሰራጭቷል።

ትላንት ከትላንት ወዲያ ሻቢያ ድጋፍ ከሰጠን የኢትዮጵያን ጥቅም ሳናሰነካ ነጻነታችንን ጠብቀን ለኢትዮጵያ አንድነትና ለህዝቧም ነጻነት እንታገላለን ብለው የተነሱትን እነ ኮሎኔል ታደሰን ወጣት ጌታቸውንና ሌሎችንም መዳረሻቸውን እንዳጠፋ ሁሉ "አፋር ኢትዮጰያዊነቱን ነብር ኾንጉርጉርነቱን " እንደማይቀይር ጠንቅቶ የሚያውቀው ሻቢያ ባሉባልታ አስመስሎ የአንዳርጋቸው መታሰር የፈጠረውን ቁጣ እንዳጋጣሚ ተጠቅሞና አዛኝ መስሎ ከፋፋይ መርዙን ዘራ። የአፋርን ህዝብ ከሌላው ኢትዮጰያዊ ሊለየው ሞክረ. ። ሻአቢያ በአንድ ድንጋይ ብዙ ወፎችን ለመግደል ሞክረ:: ከዚህ በሗላ በተጠቀሰው የአፋር ድርጅት ላይ ሻቢያ ሊወስድ የሚችለውን እርምጃ መገመት አይከብድም። ሌሎችም ደግሞ ከዚህ ድርጅት ጋር እንዳይተባበሩ የሚያሳድረውን ተጽእኖ መገመት ይቻላል።

ይህ ሁኔታ የሻቢያ “አለሁላችሁ ባይነት” ና “የኢትዮጵያ አንድነት ያሳስበኛል “ ሲል ምን ማለቱ እንደሆነ በተግባር የሚያሳይ ነው”። አሁን ሁሉንም ኢትዮጰያዊ ፊት ለፊት ማስከፋት እንደማይችል የተገነዘበው ሻቢያ የጥቃት ኢላማወች አፋሮች ሆነዋል፡፥ባንድ በኩል፥ “ኢትዮጵያዊነት ናፈቀኝ” ለማለት የሚዳዳው ሻቢያ፣ አፋሮች በቀጣይነት ኢትዮጵያዊነትን ስለመረጡ የቅጣት ዱላ ያወርድባቸዋል። በአፋሮች ላይ የሚሰነዘረው የሻቢያ ዱላ በሁሉም ለአንድነት የቆመ ኢትዮጵያዊ ላይ የተሰነዘረ ዱላ ነው።

ዛሬ አፋሮች የኢትዮጵያዊነትና የአንድነት ሰሜት የሚያስከፍለውን ዋጋ ሁሉ በሁሉም ኢትዮጵያዊያን ስም እየከፈሉ ነው።አፋሮች እንደ ቀደምት አባቶቻችንና እናቶቻችን ሁሉ የባለጉልበቶች ግፍ በዘመናት ታሪክ የተገነባውን አንድነት በቀላሉ እንደማያፈርስው ለሁሉም ምሳሌ ሆነዋል። አፋሮች ለሚወዷት ኢትዮጵያ እየታሰሩላት፣ እየተሰደዱላት፣ እየተገደሉላት ነው።

ቀደም ባለው ጊዜ የኢትዮጵያና የኤርትራ 50 አመታት ተለያይቶ እንደገና አንድ መሆናቸው በዘመናት ሂደት የተገነባውን የህዝብ ቁርኝት እንዲህ በቀላሉ ማፈራረስ እንደማይቻል አሳይቶናል። ይህ የሆነውም በጊዜው በነበሩ ባለራእዮች ያልታከተ ትግል ነው። ዛሬ ደግሞ ይህን የተላለፈልንን የታሪክ ቅርስ ለማስከበር እያንዳንዱ የፖለቲካ መሪም ሆነ ዜጋ ምን እያደረገ እንደሆነ ጊዜ ያሳየናል ታሪክም ይመዘግበዋል።

ይህን ካልኩ ሻአቢያ የኢትዮጵያን ህዝብ የትግል አጀንዳ ለመቆጣጠር ትኩረቱንም ለማስቀየር ከሚያካሂዳቸው ቀጥተኛ ጥቃቶች በተጨማሪ  የሚገፋቸው አጀንዳወችና ከሚያካሂዳቸው ተግባሮች ውስጥ አንዳንዶቹን እንመልከት

## አሾህን በሾህ የሚለው የሻአቢያ አስትራተጇ

በረዥም ታሪኩ ውስጥ ሻአቢያ የሚፈልገውን አጀንዳ ተግባራዊ ለማድረግ ሁለት ዋና ዋና ስትራተጂዎችን ይከተላል፥

### 1. ኢትዮጵያዊ ድርጅቶች በተለያየ መንገድ አጀንዳውን እንዲቀበሉት በማድረግ ከኢትዮጵያዊያን የሚነሳ ተቃውሞን ለማለሳለስ ይጥራል::

ይህን ጉዳይ  በትክክል ለመረዳት እጅግ ብዙ መረጃዎችን ማቅረብ ቢቻልም በጣም ግልጽ የሚሆነው ግን የኤርትራን መገንጠል እውን ለማድረግ  ከኤርትራ ውጭ በሚገኘው ኢትዮጵያዊ ውስጥ ሻቢያ “የራስን እድል በራስ መወሰን እስከመገንጠል” የሚለው አጀንዳ በሰፊው እንዲስፋፋ ያካሄደው ስራ በዋናነት የሚጠቀስ ነው።

የኢትዮጵያ ተማሪዎች እንቅስቃሴ ባብዛኛው አጅግ በሚገርም ሁኔታ የኢትዮጵያን ታሪክ፣ የኢትዮጵያን አንድነትና ሉአላዊነት እጅግ ዝቅ አድርጎ  እንዲያይ ሀገሪቱ ባጠቃላይ “እስርቤት” እንደሆነች “አምኖ” ከዚህ እስር ቤት ለመላቀቅ ደግሞ “ የራስን እድል በራስ መወሰን እስከመገንጠል” አስፈላጊ ነው ፣ ኢትዮጵያን አፈራርሶ መገጣጠም አስፈላጊ ነው የሚለውን አጀንዳ አንግቦ ከዩኒቨርስቲ እስከ አንደኛ ደረጃ፣ ከሀገሪቱ ዋና ከተማ እስከ ድንበር መንደሮች ድረስ፣ ከመንግስት ቢሮክራቶች እስከ ወዛደርና ገበሬ ተቀባይነት እንዲያገኝ እጅግ ሰፊ ስራ ሰርቷል። ከዚህም ጋር ተያይዞ የሻቢያና የጀበሀን ትግል “ፍትሀዊ የነጻነት ትግል” ነው በማለት እጅግ ብዙ ለውጥ ፈላጊዎች እንዲቀበሉት ብቻ ሳይሆን ፣ ለዚህም እንዲታገሉ ተደርጓል። ይህ ሁሉ ሲሆን ግን ከሻቢያን ጋር የተዛመደው የጥፋት አደጋ በበቂ እንዲነገርና ህዝብ እንዲያውቀው አልተደረገም ነበር።

ይህን በተመለከተ በጊዜው ጎልተው ይታዩ የነበሩ የተለያዩ ለውጥ ፈላጊ ሀይሎች በመላ ሀገሪቱ ያሰራጩትን ፕሮፓጋንዳ እንዲሁም ወያኔ የትግራይን ህዝብ የነ አጼ ዮሀንስንና የአሉላ አባነጋን ተጋድሎና የኢትዮጵያ  ዳር ድንበር ቀይ ባህር ነው በማለት ያካሄዱትን ታላቅ ጀብዱ ወደጎን ትቶ ኤርትራን በኢትዮጵያ ቅኝ የተገዛች እንደሆነች ተቀብሎ ያላንዳች ጥያቄ ህዝብ የመገንጠል እንቅስቃሴውን እንዲደግፍ ማድረጉን ለዚህም የትግራይ ወጣት ደም እንዲገብር መደረጉን በአብነት መመልከት እንችላለን።

ይህንን በተመለከተ ከተሰሩት ታላለቅ ስህተቶች ውስጥ ስለ አንዱ የሻቢያ ሚና ምን እንደነበረ የሕወሀት የቀድሞው ከፍተኛ አመራር አባል የነበሩት አቶ ገብሩ አስራት እንደሚከተለው ይገልጹታል "ተሀሀት በ1968 ባሳተመውና ባሰራጨው ማኒፌስቶ የኤርትራን ቅኝ ግዛትነት የመቀበሉ ትንታኔ በእውነተኛ ታሪካ ላይ ያልተመሰረተና በጥልቀት ያልተጠና ከመሆኑም ባሻገር እንዳለ ሻአቢያወች የሚሉትን ሁሉ የሚቀበል ነበር። በወቅቱ ተሀሀት የወሰደው አቋም በዋናነት ይከተለው ከነበረው ርእዮተ አለም የመነጨ ቢሆንም ሻአቢያወች ያሳደሩበት ተጽእኖ ቀላል አልነበረም"" (ገብሩ አስራት፤ ሉአላዊነትና ዲሞክራሲ በኢትዮጵያ ፣ 2006 አ.ም፣ ገጽ 61.)

የኤርትራ ግንባሮች የኢትዮጵያ ታጋዮችን እንቅስቃሴ ለራሳቸው መጠቀሚያ ለማድረግ ያደረጉትን መረባረብ በተመለከተ ደግሞ ጴጥሮስ ተሰፋ ጊዮርጊስ እንደሚከተለው ይላል "ተራማጁ የኤርትራ ተማሪዎች እንቅስቃሴ የኢትዮጰያን ፊውዳላዊ ስርአት በሶሺያሊስት ስርአት ቢተካ የኤርትራም ችግር በሰላማዊ መንገድ የራሱን እድል በራስ በመወሰን መተክል ይፈታል ብሎ ያምን ነበር። ይህም በመሆኑ በኢትዮጵያውያን ተማሪወች ትግል ውስጥ የነጻነት ተስፋ ስለታያቸው እጅግ የነቃ ተሳትፎን ያደርጉ ነበር" https://mestawot.wordpress.com/2008/04/15/the-student-movement-part-2/

አሁን ባለው ሁኔታ ደግሞ በተለይም ካለፉት ጥቂት አመታት ወዲህ ሻቢያ ከደረሰበት ኪሳራና፣ በአለም አቀፍ ህብረተሰቡም ከደረሰበት ማእቀብና መገለል ለመላቀቅ በሚያደርገው ሩጫ በዋናነት እየተጠቀመ የሚገኘው በኢትዮጵያውያን ሆኗል፡ ስለ ስርአቱ ቅን አሳቢነት፣ ስለ ኢሳያስ ሰላማዊነትና በህዝብ ተወዳጅነት፣ ስለ ኢሳያስ የልማት እቅድ (አምነውበትም ይሁን በሌላ ምክንያት) የሚናገሩት አለም አቀፍ ማእቀብ እንዲነሳለት በሰልፍ፣ በጽሁፍና በመሳሰሉት በድፍረት የሚንቀሳቀሱት የሻቢያ ሰወች ብቻ ሳይሆኑ ሌሎች ኢትዮጵያውያንም ሆነዋል። በሚገርም ሁኔታ በኢትዮጵያውያን አካባቢ ፣ ሻቢያን በተመለከተ ወደሗላ ተመልሰን ታሪክ እንዳናነሳ ወይም ደግሞ ውደፊት ተመልክተን ሊመጣ የሚችለውን አደጋ እንዳንመረምር ተጽእኖ ሊያደርጉ የሚሞክሩት የራሳችን ወገኖችም ጭምር ሆነዋል ። ነገና ከነገ ወዲያ ደግሞ ከዚህ የባሰ ነገር ብንመለከት ወይም ብንሰማ የሚያስገርም አይሆንም።

## 2. ትጥቅ አስፈች ፕሮፖጋንዳና የስነ ልቦና ውጊያ

ቀደም ሲል ሻቢያ ይጠቀምበት የነበረው ታክቲክ የራሱን ሀይል እጅግ አግዝፎ የኤርትራ ተዋጊዎች እጅግ የተለየ ችሎታ ያላቸው፣ በየተራራው ስር ልዩ ፋብሪካ፣ ልዩ የፈጠራ ውጤትን እያስመዘገቡ ተአምር እየሰሩ እንደሆነ አስመስሎ በማውራት የኤርትራ ጉዳይ "ያለቀለት ጉዳይ ነው" " "ሁሉም የተቀበለው ነው" "እነሱ አይቻሉም" በማስባል በኢትዮጵያዊው አስተሳሰብ ውስጥ "ለማይሆን ነገር ለምን እለፋለሁ" የሚል ተሰፋ መቁረጥ እንዲሰፍን ማድረግ ነበር ። በደርግ ጊዜ ይህን አስተሳሰብ በሰፊው እንዲስፋፋ ሻቢያ እጅግ ሰፊ ጥረት አድርጓል። ህወሀትም ተባብሮታል።

አሁን ባለው ሁኔታ ደግሞ የሻቢያ የፕሮፓጋንዳ ትኩረት ኢትየጵያውያን የኤርትራን "ነጻ" ሀገርና መንግስትነት "ያለቀለት ጉዳይ" አድርገን እንድንቀበል እና ምንም አይነት የይገባኛል ጥያቄ በኢትዮጵያውያን ዘንድ እንዳይነሳ ማድረግ ነው።

ይህን ለማድረግ ቀደም ሲል መለሰ ዜናዊ፣ "ኤርትራን ማስመለስ ከቻላችሁ መንገዱን ጨርቅ ያድርግላችሁ" በማለት ገና ከጅምሩ የኢትዮጵያ ህዝብ ተስፋው እንዲጨልም የስነልቦና ሰለባ አካሂዷል።

አሁን ደግሞ ሻቢያ በኢትዮጵያውያን ዘንድ ኤርትራን በተመለከተ ጭለምተኝነት እና ተስፈ መቍረጥ እንዲስፋፋ እያደረገ ያለው " የአፍሪካ አንድነትና የተባበሩት መንግስታት ለኤርትራ ነጻነት እውቅና ሰጥተዋል ስለዚህም ምንም

ማድረግ አይቻልም" "ከተገነጠሉ 24 አመት ሆኗቸዋል ስለዚህም ምንም ማድረግ አይቻልም" የሚል ላይ ላዩን ሲያዩት እውነት የሚመስል ትጥቅ አስፈች ፕሮፓጋንዳ በማስራጭት ነው።

እጅግ የሚገርመው ከላይ እንደገለጥኩት "የራስን እድል በራስ መወሰንና ፡የኤርትራ ትግል ፍትሀዊ ነው" የሚለውን አጀንዳ ተቀባይነት እንዲያገኝ ከኤርትራ ውጭ የነበሩ ብዙወቹ ተቃዋሚዎች እንዳደረጉት ሁሉ ዛሬም "የአፍሪካ አንድነትና የተባበሩት መንግስታት እውቅና ሰጥተውታል ስለዚህም ምንም ማድረግ አይቻልም" የሚለውን ትጥቅ አስፈች አጀንዳ የራሳችን ሰዎች ሲያስተጋቡት ማየት " ሰው ካለፈው ስህተቱ እንዴት አይማርም" የሚያስብል አሳዛኝ ጉዳይ ነው።

ለማንኛውም እውን አንድ ሀገር "በአፍሪካ አንድነት ድርጅትና በተባበሩት መንግስታት እውቅና ስለተሰጠው "ሁሉም የግድ መቀበል ይኖርበታል? ሌሎች ሀገሮችስ የሚያነሷቸውን የይገባኛል ጥያቄወች ውድቅ ያደርግባቸዋልን? እስኪ መንግስታትን እውቅና የመስጠትና ያለመስጠት ጉዳይን በቅርበት እንመልከት፡

## ያፍሪካ አንድነትና የተባበሩት መንግስታት ድርጅቶች እውቅና ጉዳይ

አንድን ሀገር ወይም መንግስት እውቅና የመስጠት ወይም ያለመስጠት ጉዳይ የየሀገሩ መንግስታት ወይም ድርጅቶች ታሪካቸውን፤ ህግን፣ ጥቅማቸውንና እስትራተጂያዊ ግባቸውን አገናዝበው የሚወስዱት እርምጃ እንጂ ግዴታ ያፍሪካ አንድነት ድርጅት ወይም የተባበሩት መንግስታት ስለተቀበሉት (እውቅና ስለሰጡ ) ሁሉም ሊቀበለው የሚገባ ጉዳይ አይደለም። ይህ ደግሞ በሻቢያ መንግስትና በኢትዮጵያውያን የተጀመረ ሳይሆን በብዙ ሀገሮች ውስጥም የሚታይ እውነታ ነው። ለምሳሌም የሚከተሉትን ማንሳት ይቻላል""

የኢስራኤል መንግስት ከተመሰረተበት ከአውሮፓውያን አቆጣጠር 1948 ጀምሮ ከሰላሳ በላይ መንግስታት እስካሁን እውቅናን አልሰጡትም። ከሞላ ጎደል ሁሉም የአረብ ሊግ አባላትና አብዛኞቹ የአስልምና ትብብር ( Organisation of Islamic Cooperation) አባላት በዚህ ውስጥ የሚጠቀሱ ናቸው።

ለምሳሌ ሞሮኮ፣ አልጀሪያ ኒጀር፣ ማሊ፣ ጊኒቢሳዋ፣ ሊባኖን፣ ኢራቅ፣ ኢራን፣ ሶሪያ.፡ ሱዳን፣ ኩዌት፣ ኦማን፣ ማሌዥያ፣ ኢንዶኔዤያ፣ ባንግላዴሽ፣ አፍጋኒስታን፣ ሰሜን ኮሪያ፣ ቦሊቪያ ፣ ሳውዲ፣አረብያ፤ ባህሬን፣ ወዘተ እስካሁን ለእስራኤል እውቅና አልሰጡም። ሁሉም ደግሞ የተባበሩት መንግስታት አባል ሀገሮች ናቸው።

ከዚህ በተጭማሪ የሚከተለው መረጃ እንደሚያሳየን እውቅና ያልተሰጣጡ ሌሎችም ሀገሮች አሉ:

| የሀገሪቱ ሰም | እውቅና ያላገኘችው በነማንና በስንት ሀገሮች ነው? | ልዩ ሁኔታ |
|---|---|---|
| የኮሪያ ዴሞክራቲክ ሪፐብሊክ (ሰሜን ኮርያ) | በጃፓን እና ደቡብ ኮሪያ እውቅና አልተሰጣትም | ከ 1948 ጀምሮ ነጻ ሀገር ሆናለች የተባበሩት መንግስታትም አባል ነች |
| የኮርያ ሪፐብኪል (ደቡብ ኮሪያ) | በሰሜን ኮርያ እውቅና አልተሰጣትም፣ | ከ 1948 ጀምሮ ነጻ ሀገር ሆናለች የተባበሩት መንግስታትም አባል ነች |
| የሰሀራ አረባዊ ዴሞክራቲክ ሪፐብሊክ | እስካሁን 39 መንግስታት ለሰሀራ አረባዊ ዴሞክራቲክ ሪፐብሊክ እውቅና አልሰጡም | ከ 1976 ጀምሮ ነጻነት አውጃለች ያፍሪካ አንድነት ድርጅትም አባል ሀገር ነች ሞሮኮ በሰሀራ አረባዊ ሪፐብሊክ ላይ የግዛት ይገባኛል ጥያቄ አላት፡ |

| | | |
|---|---|---|
| የአርሜንያ ሪፐብሊክ | በፓኪስታን መንግስት እውቅና አልተሰጣትም | ነጻነት ያወጀችው ባውሮፓ አቆጣጠር ከ 1991 ጀምሮ ነው |
| የቻይና ሪፐብሊክ (ታይዋን) | ከ 1949 ጀምሮ ነጻ መንግስት ነኝ ያለች ቢሆንም እስካሁን ከ 21 መንግስታት እና ከቫቲካን ሌላ በሌሎች ዘንድ እውቅና አልተሰጣትም፣ | ኮሚኒስት ቻይና አሁንም ታይዋን የኔ ግዛት ናት ትላለች። |
| የሳይፕረስ ሪፐብሊክ | እስካሁን በተርኪ እና በሰሜናዊ ሳይፕረስ በድንበር አለመስማማት ምክንያት እውቅና አላገኘችም | ከ 1960 ጀምሮ የተባበሩት መንግስታት አባል ሀገር ነች |

https://en.wikipedia.org/wiki/List_of_states_with_limited_recognition#UN_member_states_not_recognised_by_at_least_one_UN_member

በነጻነት ትግል ላይ እያሉ ለተለያዩ መንግስታት እውቅናን ያልሰጡትን ስንመለከት ደግሞ ዝርዝሩ እጅግ ብዙወችን ያጠቃልላል። ባፍሪካ አንድነት ድርጅቶችም ሆነ በተባበሩት መንግስታት አባል ሆነው አንዱ ባንዱ ላይ የግዛት ይገባኛል ጥያቄ ያላቸው ሀገሮች ደግሞ እጅግ ብዙወች ናቸው ፡ በነገራችን ላይ ሶማሌ በኦጋዴን ላይ ያላትን የግዛት ጥያቄ እንካሁን እንደያዘች እንደሆነ መገንዘብ ያሰፈልጋል።

ይህ ሁኔታ የሚያሳየን እያንዳንዱ ሀገር ወይም ድርጅት ለሌላው እውቅና የሚሰጠው (ወይም የግዛት ይገባኛል ጥያቄ የሚያነሳው) የራሱን ልዩ ሁኔታ፣ ሀገራዊ ጥቅሙናና እስትራተጂያዊ (የረጅም ጊዜ) ግቡን በመመርመር እንጂ አለም አቀፍ ድርጅቶች ስለተቀበሉት ወይም ስላልተቀበሉት እንዳልሆነ ነው። በርግጥ የአለም አቀፍ ድርጅቶች አመለካከት አንድ ድርጅት በሚወሰደው እርምጃወች ውስጥ በግንዛቤ ውስጥ መግባት ቢኖርበትም ሀገራዊ ራእይንና የሀገርን የረጅም ጊዜ ጥቅም ገደል እስከመወርወር ሊያደርስ እንደማይገባ ግን ቀደም ያሉት የኢትዮጵያ (ኤርትራን ጨምሮ) አርበኞች ታሪክና የብዙ ሀገሮች ተመክሮ ያሳየናል።

በሀገራችን የተለየ ሁኔታ ውስጥ የባእዳንን እውቅና በለመለከተ ሌላው የሚነሳው ተዛማጅ ጥያቄ አንድ ህዝብ በጉልበትም በሌላም ህልውናውን የሚነካ ነገር ሲፈጸምበት ባእዳን ስለተስማሙ ውሳኔውን መቀበል ይኖርበታል ወይስ እምቢ ብሎ መታገል ይገባዋል? የሚለው ነው። ለምሳሌ ወያኔ/ኢህአዴግ ለሱዳን የስጠውን መሬትስ የኛ ነው ይገባናል ብለን መጠየቅ ይኖርብናል ወይስ ሁለቱ መንግስታትና አለም አቀፍ ድርጅቶች ስለተቀበሉት ነጭ ባንዲራ አውለብልበን መቀበል ይኖርብናል? ይህ አያንዳንዳችን ነገ ሳይሆን ዛሬ ልንመልሰው የሚገባን ጉዳይ ይመስለኛል።

አንድ ነጻ ህዝብ ወይም ነጻ ሀገር የራሱን ጥቅም የሚያስጠብቅ አቋምና እርምጃ መውሰድ የራሱ ተግባር ነው። የአንድ ፖለቲካ ድርጅት ህላፊነትና ብቃት የሚመዘንበት አንዱ ነጥብ ደግሞ ሀገራዊ ጥቅምን በተመለከተ በሚያሳየው ራእይ ነው። ራእይ የሌለው ድርጅትና ህዝብ ወይም ባጭር ጊዜ የፖለቲካ ጠቀሜታ ላይ ብቻ አተኩሮ የሚወስድ እርምጃ ግን መጨረሻው ጥፋት ነው። በአንዱ የሀገራችን ክፍል የደረሰን የህልውና መናጋት በሰበብ ባስባቡ ተቀብለን በሌላው የሀገራችን ክፍል የሚነሳን ተመሳሳይ ጥያቄን ለመቃወም መሞከር የማያዋጣ ጉዞ ነው።

## ማጠቃለያ

ኢሳያስ አፈወርቂና ሻቢያ የሚወስዱት እርምጃ ሁሉ የራሳቸውን ጊዚያዊና የረጅም ጊዜ ጥቅም በግንዛቤ ውስጥ ያስገባ ነው። የህ ደግሞ ካትዮጵአ መሰረታዊና ስታራተጂያዊ ጥቅም ጋር የሚፓረር ነው። በመሆኑም ይህን

በተመለከተ ልንመልሰው የሚገባው ጥያቄ ኢሳያስ ስለ ኢትዮጵያ መልካም ነገር ለምን አያስብም ሳይሆን እኛ የኢዮጵያንና የህዝቧን የአጭርና የተጅም ጊዜ ጥቅም በተመለከተ እያሰብን እና እየሰራን ያለነው ምንድነ ነው የሚለው ነው።

ሀገራችን በሁለት አጣብቂኝ ጉዳዮች መሀል ትገኛለች። ለ24 አመታት የህወሀት/ኢህአዴግ አግላይ የግፍ ስርአት እጅግ አይን ባወጣ መልክ አሰቃቂ ተግባር እየፈጸመ በመሆኑ የኢትዮጵያ ህዝብ እጅግ መርሮታል።ከዚህም የተነሳ “የፈለገው ይምጣ” ወደሚል መደምደሚያ እየደረሱ ያሉ ብዙወች ናቸው። በሌላ በኩል ይህን ብሶት ወዳጅ መስሎ ለእኩይ ተግባሩ፣ ለጸረ ኢትዮጵያ ግብ ሊጠቀምበት ኢትዮጵያን እንደገና ለመግደል አሰፍስፎ የሚጠብቀው በዋናነት ሻቢያ ነው። ወቅቱ ለሀገራችን ለህዝባችንና ለአንድነት ሀይሎች እጅግ ፈታኝ ነው፡፡ የአፋር ህዝብ አበሳ የሚያሳየውም ይህንኑ ነው። ይህን ፈተና በእርጋታ በጥበብ፣ በሰፊ ራእይና አርቆ አሳቢነት በትብብር በኢትዮጵያዊ መግባባት መወጣት የግድ ነው። ይህን ለማድረግ ደግሞ ከባእድ ተጽእኖ ነጻ ሆኖ የሚነቃነቅ ኢትዮጵያዊ የጋራ ሀይልን የግድ ይላል፡ በታሪክ ውስጥ በተለያየ ምክንያት አንድ ጊዜ መሳሳት ቢኖርም ተመሳሳይ ስህተትን ደግሞ ደጋግሞ መፈጸም ግን ይቅር የማይባል ነው። አንዱ የባለራእዮችና ያርቆ አሳቢ መሪወች መመዘኛም ይኸው ነው፡፤

ኢትዮጵያ ለዘላለም ትኑር።

አስተያየትወን ለጸሀፊው ለማድረስ በሚከተለው አድራሻ ይጻፉ: ethioandenet@bell.net